መልእክት አምስት

## የከነዓን ምድር ፍሬ እና
## የመልካሚቱ ምድር ድርሻን የመከፋፈል
## ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ኢያ. 5፡12፤ 13፡1—22፡34፤ ቆላ. 1፡12፤ ሐዋ. 26፡18

**I. የእስራኤል ልጆች ወደ ከነዓን ምድር ከገቡ በኃላ መናው አቆመ፤ ከዚህ በኋላ መና አልነበረም፣ ነገር ግን የከነዓንን ምድር ፍሬ በሉ—ኢያ. 5፡12፦**

ሀ. ሕዝቡ የምድሪቱን ምርት መመገብ ሲጀምሩ መናው መቆሙ የምድሪቱ ፍሬ የመናው መቀጠል እንደነበረ ያመለክታል።

ለ. በምድረ በዳ ሲቅበዘበዙ ሳለ እስራኤል የበሉት መና (ዘጸ. 16)፣ በተመጋቢዎቹ በኩል ምንም መድከም የማይጠይቀውን ለተመረጠው ሕዝቡ በእግዚአብሔር በቀጥታ የተሰጠውን ክርስቶስ እንደ ሰማያዊ ምግብ በምሳሌ ያሳያል።

ሐ. በከነዓን በነበራቸው ውጊያ በእግዚአብሔር ለእስራኤል የተሰጠው የተስፋይቱ ምድር የበለጠገ ምርት ለአማኞች የተሰጠውን በክርስቶስ ላይ እንዲደክሙ የሚጠይቃቸውን ክርስቶስን እንደ የተጠናቀቀው የሕይወት አቅርቦት በምሳሌ ያሳያል—ዘዳ. 8፡7-10፦

1. እዚህ ጋር በምሳሌ እንደ እንደተገለጸው፣ ክርስቶስን እንደ ምድራችን የራሳችን ካደረግነው በኋላ፣ ምግባችን፣ የሕይወት አቅርቦታችን የሚሆንን ነገር ለማፍራት በእርሱ ላይ መድከም ያስፈልገናል።
2. እንደ መልካሚቱ ምድር ምርት ክርስቶስን ስንበላው እና ስንደሰተው፣ ከክርስቶስ ጋር በሕይወት፣ በባህርይ እና በመገለጥ አንድ እየተደረግን በእርሱ እየተቀናበርን ነው—ዮሐ. 6፡57፤ ፊልጵ. 1፡19-21።
3. በመጨረሻም፣ ክርስቶስን እንደ ርስታችን፣ ሃብታችን መደሰታችን የእግዚአብሔር ርስት፣ የእግዚአብሔር ውድ መዝገብ እና ሃብት አድርጎ ያቀናብረናል—ኤፌ. 1፡11-14፣ 18፤ ተዛ. ዘጸ. 19፡5።

መ. በግብጽ፣ በምድረ በዳ፣ እና በመልካሚቱ ምድር የእስራኤል ሕዝብ ሦስት የመብላት ደረጃዎችን ተለማምደዋል፦

1. በግብጽ የእስራኤል ሕዝብ የፋሲካውን በግ በሉ—12፡3፣ 8-9፦
   ሀ. የፋሲካው በግ የተጠበሰው ሥጋ ለሕይወት አቅርቦት እንደሚበላው እንዲሁ፣ ለሕይወት አቅርቦታችን ክርስቶስን መብላት አለብን—ቁ. 8-10፤ ዮሐ. 6፡53፣ 55-57፦
      1) የሰውን ውድቀት ችግር ለመፍታትና የእግዚአብሔርን የመጀመሪያ ውጥን ለመፈጸም፣ ሕይወትና ቤዛነት ሁለቱም ያስፈልጋሉ።
      2) በክርስቶስ ደም በኩል የሆነው የእግዚአብሔር ፍትሃዊ ቤዛነት ለሕይወታዊ መዳናችን ክርስቶስን እንደ ሕይወት ለማደል ወደ ሆነው የእግዚአብሔር ግብ የሚያደርስ የክንውን ሂደት ነው—ሮሜ 5፡10።
   ለ. የእስራኤል ልጆች የፋሲካውን በግ ከራሱ፣ ከእግሮቹ እና ከውስጥ ክፍሎቹ ጋር መብላት ነበረባቸው—ዘጸ. 12፡9፦
      1) ራስ ጥበብን ያመለክታል፣ እግሮች ድርጊትን እና እንቅስቃሴን ያመለክታሉ፣ የውስጥ ክፍሎች፣ አእምሮውን፣ ስሜቱን፣ ፈቃዱን እና ልቡን ከሁሉም አገልግሎታቸው ጋር ጨምሮ የክርስቶስን ማንነት የውስጥ ክፍሎች ያመለክታሉ።
      2) የፋሲካውን በግ ከራሱ፣ ከእግሮቹ እና ከውስጥ ክፍሎቹ ጋር መብላት ሙሉውን ክርስቶስ ከጥበቡ፣ ከድርጊቱና እንቅስቃሴው፣ እና ከውስጥ ክፍሎቹ ጋር ወደ መውሰድን ያመለክታል—ዮሐ. 6፡57፤ 1 ቆሮ፣ 1፡24፤ ራእ. 14፡4፤ ፊልጵ. 1፡8።
2. በምድረ በዳ የእስራኤል ሕዝብ መና በሉ—ዘጸ. 16፡14-16፣ 31፤ ዘኁ. 11፡7፦
   ሀ. ለሕዝቡ መና እንዲበሉ በመስጠቱ፣ እግዚአብሔር ውጥኑ ምግባቸውን በመቀየር ቅንብራቸውን መቀየር እንደነበር አመልክቷል—ዘጸ. 16፡14-15፦
      1) በስም የእስራኤል ልጆች ግብፃውያን አልነበሩም፣ ነገር ግን በባህሪ እና በቅንብር ፈጽሞ ከግብፃውያን የተለዩ አልነበሩም—ቁ. 3።
      2) የግብፃውያን ምግብ እርካታን ለማግኘት መመገብ የምንፈልጋቸውን ነገሮች በሙሉ ያመለክታል—ዘኁ. 11፡4-6።
   ለ. እግዚአብሔር የተዋጀው ሕዝቡ የግብጻዊያን ምግብ እንዲረሱና ሰማያዊውን ምግብ እንዲመገቡ ፈልጎ ነበረ—ዘዳ. 8፡3፦

1) አብዝተን መናውን ስንበላ፣ ይበልጥ እግዚአብሔርን እንመስላለን፣ ከእርሱ ጋር አንድ እንሆናለን፣ እርሱ በሆነው መሠረትም እንኖራለን እንመላለስማለን።

2) ከጌታ ጋር ባለን የእለት ኑሮ በእጅጉ የሚረዳን ነገር ክርስቶስን እንደ ሰማያዊው ምግብ መብላት ነው፤ ክርስቶስን በመብላት ክርስቶስን እንሆናለን፤ ይህም ማለት፣ ክርስቶስ ቅንብራችን ይሆናል ማለት ነው—ዮሐ. 6፡56-58።

3. በከነዓን የእስራኤል ሕዝብ የመልካሚቱን ምድር ምርት በሉ—ኢያ. 5፡11-12፡-

ሀ. በሦስተኛው የመብላት ደረጃ፣ የመልካሚቱን ምድር የበለጠገ አቅርቦት በሉ፣ ይህም ድል-ነሺ ይሆኑ ዘንድ የበለጠ አቀናበራቸው።

ለ. መልካሚቱ ምድር ስንዴ፣ ገብስ፣ ወይን፣ በለስ፣ ሮማን፣ ዘይት ያሏቸው የወይራ ዛፎች እና ማር ያሉባት ምድር ነበረች፤ እነዚህ ሁሉ ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ብልጥግናዎች በምሳሌ ያሳያሉ—ዘዳ. 8፡8፤ ኤፌ. 3፡8።

ሐ. የመልካሚቱን ምድር ብልጥግናዎች በመደሰት፣ የእስራኤል ሕዝብ በምድሩ ላይ የነበሩትን ነገዶች አሸነፉ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት መሠረቱ፣ በምድር ላይ እንዳለ የእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ መቅደሱን ገነቡ—ኢያ. 5፡11-12።

4. እነዚህ ሦስት ደረጃዎች ክርስቶስን በመብላት የአማኞችን ድሰታ ሦስት ደረጃዎች በምሳሌ ያሳያሉ—ዮሐ. 6፡51-57፤ 1 ቆሮ. 5፡7-8፤ 10፡3-4፤ ፊልጵ. 1፡19፡-

ሀ. በመጀመሪያዎቹ ሁለት ደረጃዎች ባለው መብላታቸው፣ አማኞች ዓለምን ትተው ለመውጣት ሃይል ያገኛሉ እንዲሁም ሰማያዊው ንጥረ-ነገር በሆነው ክርስቶስ ይቀናበራሉ—ዮሐ. 6፡51-57፤ 1 ቆሮ. 5፡7-8፤ 10፡3-4።

ለ. የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ግብ ጋር ለመድረስ፣ መንፈሳዊ ጠላቶችን ድል-እንድንነሣ፣ የእግዚአብሔር ማደሪያ ለመሆን እንድንገነባ እና የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር እንድንመሠርት ክርስቶስን እንደ መልካሚቱ ምድር የበለጠገ ምርት ወደ መብላት ከፍተኛው ደረጃ እስክንገባ ድረስ መገስገስ አለብን።

ሐ. ክርስቶስን እንደ መልካሚቱ ምድር ምርት ስንበላው፣ በእርሱ እንቀናበራለን፣ ለቤተ ክርስቲያን እንደ ክርስቶስ አካል መገንባት ከክርስቶስ ጋር በሕይወት፣ በባህርይ እና በመገለጥ አንድ እንሆናለን—ኤፌ. 4፡16።

**II. የመልካሚቱ ምድር ድርሻን የመከፋፈል ውስጠ-መሠረታዊው ትርጉም ምድሪቱን የራሳችን የምናደርገው እኛ አንዱን ክርስቶስ በተለያዩ መንገዶች እንደምንለማመደው ነው—ኢያ. 13፡1—22፡34፡-**

ሀ. በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ ከምድሪቱ ድርሻን መከፋፈል የሚባል ነገር አለ—ቆላ. 1፡12።

ለ. ኢያሱ ምድሪቱን ከያዘ በኋላ፣ እግዚአብሔር የተያዘውን ምድር እንዲሁም ገና ያልተያዘውን ምድር እንኳን ሳይቀር እንዲያከፋፍል አዘዘው ምክንያቱም በእግዚአብሔር ዓይኖች ምድሪቱ በሙሉ ለእስራኤል ነበረችና—ኢያ. 13፡6፡-

1. እግዚአብሔር በጥበቡ መልካሚቱን ምድር በአጠቃላይ ለሁሉም የእስራኤል ልጆች አላከፋፈለም፤ ይልቁንም፣ ያችን ምድር፣ ማለትም፣ ክርስቶስን ለተለያዩ ነገዶች አከፋፈለው—ቁ. 7።

2. ነገዶቹ የተለያዩ ስለነበሩ፣ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ነገድ ተመሳሳይ ምድር፣ በተመሳሳይ መንገድ ሊሰጣቸው አልቻለም።

3. ሁሉም ነገዶች የምድሪቱ ባለቤቶች ነበሩ፣ ነገር ግን ነገዶቹ በሆኑት ነገር መሠረት የምድሪቱን ልዩ የሆነ ድርሻዎች ያዙ—14፡6-15፤ 18፡1—19፡27።

4. የዚህ የምድሪቱ እጣ ክፍፍል ምሳሌ ፍጻሜ ዛሬ በእኛ መካከል አለ— ቆላ. 1፡12።

ሀ. ሁላችንም ተመሳሳይ ክርስቶስ አለን፣ ነገር ግን ክርስቶስን የምንለማመደው በተለያዩ መንገዶች ነው—1 ቆሮ. 1፡12።

ለ. የራሳችን የምናደርገው ምድር (ክርስቶስ) እኛ በሆንነው ነገር መሠረት ነው—ሮሜ. 12፡3፣ ኤፌ. 4፡7።

ሐ. በቆላስይስ 1፡12 ጳውሎስ ስለ "ቅዱሳን ርስት" ሲናገር ሁሉን-ያካተተውን ምድር ጽንሰ-ሃሳብን ይጠቀማል፡-

1. "ርስት" የሚለው የግሪክ ቃል የእጣ ክፍፍልን በማመልከት "እጣ" ተብሎም ሊተረጎም ይችላል።

2. ጳውሎስ ወደ ቆላስይስ ሰዎች መልእክት ሲጽፍ፣ በሃሳቡ ውስጥ ለእስራኤል ልጆች መልካሚቱን ምድር በእጣ የማከፋፈል ስእል ነበረ፤ *ርስት* የሚለውን ቃል የተጠቀመው በብሉይ ኪዳን ያለውን የምድሪቱን ዘገባ እንደ መነሻ በመጠቀም ነው—ኢያ. 14፡2፡-

ሀ. በቆላስይስ ክርስቶስ እንደ ርስታችን፣ እድል ፈንታችን ተገልጧል—1፡15-19፤ 2፡6-15።

ለ. የከነዓን ምድር ለእስራኤል ልጆች ሁሉ ነገር እንደነበረ እንዲሁ፣ የመልካሚቱ ምድር ምሳሌ እውነታ የሆነው ክርስቶስም ለእኛ ሁሉ ነገራችን ነው—1፡12።

3. ክርስቶስ በሁሉ ፊተኛ ስፍራ እንዳለው እና ሁሉን እንዳካተተው ማንነት የቅዱሳን ርስት ነው—ቁ. 12።
4. የአዲስ ኪዳን አማኞች እድል ፈንታ ቁሳዊ ምድር አይደለም፤ ሕይወትን እንደሚሰጠው መንፈስ ሁሉን-ያካተተው ክርስቶስ ነው—2፥6-7፤ ገላ. 3፥14፦
   ሀ. የመልካሚቱ ምድር ብልጥግናዎች በመንፈሱ ለአማኞቹ እንደተትረፈረፈ አቅርቦት ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ብልጥግናዎች በተለያዩ ገጽታዎች በምሳሌ ያሳያሉ—ዘዳ. 8፥7-10፤ ኤፌ. 3፥8፤ ፊልጵ. 1፥19።
   ለ. የምድሪቱን ብልጥግናዎች በመደሰት፣ በክርስቶስ ያሉ አማኞች እንደ እግዚአብሔር ቤትና እንደ እግዚአብሔር መንግሥት አካሉ ለመሆን ይገነባሉ—ኤፌ. 1፥22-23፤ 2፥21-22፤ 1 ጢሞ. 3፥15፤ ማቴ. 16፥18-19፤ ሮሜ. 14፥17።

መ. በሐዋርያት ሥራ 26፥18 ጳውሎስ ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስ እንደ ርስታችን ይጠቅሳል፦

1. ዓይኖቻችን ከመከፈታቸው እና ከሰይጣን ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ከመዞራችን የተነሣ፣ የኃጢአቶች ይቅርታ ማግኘት ብቻ ሳይሆን መለኮታዊ ርስትንም ተቀብለናል።
2. ይህ ርስት ለተዋጁት ሕዝቡ ካለው ነገሮች ሁሉ፣ ካደረጋቸው ነገሮች ሁሉ፣ ከሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ጋር ሦስታንዱ አምላክ ራሱ ነው፤ ይህ ሦስታንዱ አምላክ እንደ ርስታቸው ለቅዱሳን የተሰጠ እድል ፈንታ በሆነው ሁሉን-ባካተተው ክርስቶስ አካል ለብሷል—ቆላ. 2፥9።
3. መልካሚቱ ምድር በእውነትም ለእኛ እንድ ርስታችን የተሰጠው በሂደት ያለፈውና የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ አካል መልበስ የሆነው ሁሉን ያካተተው ክርስቶስ ምሳሌ ናት—1፥12።

© 2021 Living Stream Ministry